# ጋዜጣዊ መግለጫ



አሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ
*2015/09*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

---

## የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲና የኢትዮጵያ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ እ.ኤ.አ. በ2016 በኢትዮጵያ ለሚደረገው የሥነ ሕዝብና የጤና ዳሰሳ ጥናት ስምምነት ተፈራረሙ

***የዳሰሳ ጥናቱ ከዚህ ቀደም የተካሄዱ ተመሳሳይ ጥናቶችን ያጠናክራል፤የተጓዳኝ ድርጅቶችንም አቅም ይገነባል***

***አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፤ መጋቢት 3 ቀን 2007 ዓ.ም.፡-*** የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲና (USAID) የኢትዮጵያ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ እ.ኤ.አ. በ2016 ለሚካሄደው የሥነ ሕዝብና የጤና ዳሰሳ ጥናት ዕቅድ ለማዘጋጀት የሚያስችል ስምምነት በዛሬው ዕለት ተፈራረሙ፡፡ ጥናቱ፣ ከፕሬዚዳንቱ አስቸኳይ የኤድስ እርዳታ ዕቅድ (PEPFAR) በተገኘ ከፊል ድጋፍ፣ በሥነ ተዋልዶና በቤተሰብ ዕቅድ ዝንባሌ፣የህጻናት የአመጋገብ ሁኔታ፣ለህጻናትና ለእናቶች በሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች፣በቤተሰብ ዕቅድ፣በኤች አይ ቪ ኤድስ ዙሪያ ያለ ግንዛቤና የበሽታው የስርጭት ሁኔታ ላይ ወቅታዊና ተአማኒነት ያለው መረጃ በማቅረብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በኢትዮጵያና በመላው ዓለም የሚገኙ ተመራማሪዎች፣ፖሊሲ አውጪዎችና የተለያዩ ፕሮግራሞችን የሚመሩ የሥራ ኃላፊዎች ከዳሰሳ ጥናቱ የሚገኘውን መረጃ በአጠቃላይ ጤናን በተለይም የሥነ ተዋልዶ ጤናን የተመለከቱ የፖሊሲ ውሳኔዎችን ለመወሰን፤ዕቅድ ለማውጣት፤ክትትልና ግምገማ ለመካሄድ ይጠቀሙበታል፡፡ መረጃው በሀገር አቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ጠቃሚ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የኢትዮጵያ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚያካሂደው አራተኛው ሀገር አቀፍ የሥነ ሕዝብና የጤና ዳሰሳ ጥናት በአይሲኤፍ ኢንተርናሽናል የቴክኒክ ድጋፍ የተደረገለት ሲሆን፤ኤጀንሲው የራሱን ዕቅድ አውጥቶና ሰፊ የሆነ የሥነ ሕዝብና የጤና መረጃ ሰብስቦ፣አቀነባብሮና ተንትኖ እንዲያቀርብ የሚያስችለው ነው፡፡

የኢትዮጵያ የሥነ ሕዝብና ጤና ዳሰሳ ጥናት በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ የተለያዩ ሀገራት መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ዙሪያ ለሚሠሩ ሥራዎች ድጋፍ ከሚያደርገው የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ የሥነ ሕዝብና ጤና ዳሰሳ ጥናት መርሀ ግብር በኩል የቴክኒክ ድጋፍ እያገኘ ነው፡፡ በዳሰሳ ጥናቱ ወቅት ተመሳሳይ ሥነ ዘዴዎችን በመጠቀም ጥናቶቹ ቀደም ሲል ከተሠሩትና በጎረቤት ሀገራት ከተሠሩ ጥናቶች ጋር ሊነፃፀሩና በዓለም አቀፍ እንዲሁም በቀጠና የመረጃ ቋቶች ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

በኢትዮጵያ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ዳሬክተር ዴኒስ ዌለር በፊርማ ሥነ ሥርዓቱ ላይ ሲናገሩ፣“የሥነ ሕዝብና ጤና ዳሰሳ ጥናት መርሀ ግብር በአባወራ ደረጃ ከሚካሄዱ ጥናቶች የላቀ ደረጃ የሚሰጠው ነው፡፡ በፕሮጀክት ላይ የሚሠሩ ባልደረቦቻችን መረጃ መሰብሰብ፣የመስክ ሥራና መረጃ የማቀነባበሪያ ሂደቱን ጨምሮ በየደረጃው ለእስታትስቲክስ ኤጀንሲው ድጋፍ ደርጋሉ” ብለዋል፡፡ “የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የእስታትስቲክስ ኤጀንሲው የ2016ቱ የዳሰሳ ጥናት ከተጠናቀቀ በኋላ በቀጣይ ለብዙ ዘመናት በጥናቱ ሂደት ያዳበሯቸውን ክህሎቶች ይጠቀሙባቸዋል” ሲሉም አክለው ገልፀዋል፡፡

የዳሰሳ ጥናቱ ግኝቶች ሀገሪቱ በ2015 (እ.ኤ.አ.) የሚሊኒየሙን የዕድገት ግቦች ከማሳካት አኳያ ያስመዘገበቻቸውን ውጤቶች ለመገምገም ዓይነተኛ መሣሪያ ይሆናል፡፡

መረጃ የመሰብሰብ ሥራው እ.ኤ.አ. በፌብሯሪ 2016 ይጀመራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

***